# ነወይ ስልጣኔ?

የተገነባውን መናድ መፈንቀሉ
ፍትህ ባይ ብዙሀን ተንቆ መጣሉ
በዳይና በዳይ መወነጃጀሉ
ላለፍው ይቅርታ አለመባባሉ፤.....

ወደ ኋላ ዙሮ
ዘር ማ'ዝርን ቆጥሮ፤
ቂም ዘርቶ ማብቀሉ
በደም መበከሉ፤.....

መታረዝ መጠማት - መኖር በድህነት
እያደሩ መንቅዝ ሁል ጊዜ መመፅወት፤
የራስ ማንነትን - ዜጋዊ ስብዕናን
የነፍስን አሻራ - ሞራላዊ ክብርን፤.....

መክዳት - ማስከዳቱ
ማጥፋት - ማስጠፋቱ
ሆድ አምላክ መብዛቱ፤
እየፈራረሱ - እያፈራረሱ
ትውልድን ማመሱ፤.....

ነወይ ስልጣኔ?
የዘመኑ ቅኔ?
ወይስ እጣ ፋንታ የሀበሻ ታሪክ
ማክትሚያ የሌለው የትዕይንቱ መድረክ።
--------//-------
ፊልጶስ / ሆላንድ